በኢትጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን

ትምህርተ ሃይማኖት ርትዕት

በቅዱሳት መካናትና መንፈሳዊ ት /ቤቶች አገልግሎት ማስተባበሪያ
2010 ዓ.ም.

1

ትምህርተ ሃይማኖት ርትዕት ፳፻
ዓ/ም

አርእስት ገጽ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ 2
አሜን 2
ክፍል አንድ 2
ትምህርተ ሃይማኖት 2
1. የሃይማኖት ትርጉምና ምንነት...............................................................................................................2
2. የሃይማኖትና የእምነት ልዩነት...............................................................................................................6
3. የሃይማኖት ጥቅም.........................................................................................................................6
ሠለስቱ አዕማድ................................................................................................................................. 9
3. የእምነት መመሪያዎች.....................................................................................................................9
ክፍል ሁለት 19
ትምህርተ እግዚአብሔር 19
1. ሀልዎተ እግዚአብሔር...................................................................................................................20
2. የእግዚአብሔር ስሞችና ትርጓሜያቸው...................................................................................................22
3. የእግዚአብሔር ጠባይዓት /የባሕርይ መገለጫዎች/.......................................................................................22
ክፍል ሦስት 25
ትምህርተ አዕማደ ምስጢር 25
1. ምስጢረ ሥላሴ.........................................................................................................................27
2. ምስጢረ ሥጋዌ.........................................................................................................................39
3. ምስጢረ ጥምቀት.......................................................................................................................54
4. ምስጢረ ቁርባን.........................................................................................................................58
5. ምስጢረ ትንሣኤ ሙታን................................................................................................................61
ዋቤ መጻሕፍት 72

--------- ------------ ------------ ------------ ------------------------------------------------------------ ------------ ------------ i ኛ ገጽ
ከ 33 ገጾች

ትምህርተ ሃይማኖት ርትዕት ፳፻
ዓ/ም

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን

መቅድም

በገዛ ፈቃዱ ይህንን ዓለም ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ በቸርነቱ የሚመግብ ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ስሙ የተመሰገነ ይሁን። የፍጥረታት ባለቤት እግዚአብሔር ከእጁ ሥራዎች ሁሉ መላእክትንና የሰውን ልጅ አዋቂ አድርጎ ፈጥሯል። ስለዚህም ሰው ከሁሉ ነገር አስቀድሞ የራሱን ማንነትና ፈጣሪውን በሚገባ ማወቅ ይኖርበታል ፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ይሁዳ በመልእክቱ “ ወአንትሙሰ አኃዊነ ሕንፁ ርእሰክሙ በሃይማኖት ቅድስት
- እናንተስ ራሳችሁን በሃይማኖት አንጻችሁ ኑሩ ” ብሏል፡፡ ይሁ. ፩፥ ፭ ሠለስቱ ምዕትም ትምህርተ ሃይማኖትን አስቀድሞ መማር እንዲገባ አዘዋል።ለዚህ ይረዳ ዘንድ ይህ የትምህርተ ሃይማኖት መግቢያ ተዘጋጅቷል፡፡

ይህ ትምህርተ ሃይማኖት የቀናች፣ የጎላች፣ የታወቀች የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት አስተምህሮን ይመለከታል። ሰው የሃይማኖት ትምህርት ን በሚገባ ሳይረዳ ሃይማኖት አለኝ፣ እግዚአብሔርን አውቃለሁ ለማለት አይችልም። ስለዚህ በማንኛውም የእድሜና የትምህርት ደረጃ ላይ ያለ ሁሉ እንደ አቅሙ የሃይማኖትን ትምህርት አውቆ ሊያሳውቅ ይገባዋል።

ይህ መጽሐፍ በተወሰነ ደረጃ የአብነት ተማሪዎችን መሠረት ያደረገ ነው። ዋና አላማውም በአብነት ትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎች በነገረ ሃይማኖት ራሳቸውን እንዲያንጹ፤ የሚማሯቸው ትምህርቶች (ንባብ፣ ዜማ፣ ድጓ . . . ወዘተ) ሁሉ ይህን የሃይማኖት ትምህርት የሚገልጹ መሆናቸውን እንዲረዱ፤ ሁሉም የአብነት ትምህርቶች መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆናቸውን እንዲያስተውሉ እና ኋላም በቤተ ክርስቲያን የምንገለገልባቸውንቅዳሴውን፣ ሰዓታቱን፣ ማኅሌቱን ወዘተ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በማጣቀስ ለምእመናን ማስተማር ይችሉ ዘንድ ነው።

ክፍል አንድ

--------- ------------ ------------ ------------ ------------------------------------------------------------ ------------ ------------ 1 ኛ ገጽ ከ 33 ገጾች

ትምህርተ ሃይማኖት ርትዕት ፳፻
ዓ/ም

ትምህርተ ሃይማኖት

1. የሃይማኖት ትርጉምና ምንነት
ሃይማኖት እግዚአብሔር ራሱን ለሰው ልጅ የገለጠው መግለጥ ነው፡፡ እግዚአብሔር ባሕርዩ ረቂቅ አኗኗሩ ምጡቅ ስለ ሆነ የሰውም ሆነ የመላእክት አእምሮ ተመራምሮ ሊደርስበትና ባሕርዩ እንዲህ ያለ ነው፣ አኗኗሩ ይህ ነው ወይም ይህን ይመስላል ሊለው የማይችል ነው፡፡ እርሱ በጊዜና በቦታ የማይወሰን ዘለዓለማዊና ምሉዕ ሲሆን ፍጥረት በሙሉ ደግሞ በጊዜና በቦታ የተወሰነ ስለ ሆነ ውስኑ የማይወሰነውን ሊያውቀውና በምርምር ሊደርስበት አይችልም፡፡

ሆኖም ግን ምንም እንኳ እግዚአብሔር ባሕርዩና አኗኗሩ በራሱ ብቻ የሚታወቅ ረቂቅ አምላክ ቢሆንም እኛ ፈጽሞ የማናውቀውና ስለ እርሱ ምንም ፍንጭ የሌለን ሆነን እንድንቀር አልተወንም፡፡ ከቸርነቱ የተነሣ ዓቅማችን ሊረዳው በሚችለው መጠን ማንነቱን፣ ህላዌውን፣ ባሕርዩን፣ መግቦቱን፣ ፈታሒነቱን፣ ፈቃዱን፣ … እናውቅ ዘንድ በተለያየ መንገድ ገልጦልናል፡፡ ሃይማኖት የሚባለው ይህ እግዚአብሔር በራሱ ፈቃድ እናውቀው ዘንድ ስለ ራሱ የገለጠው መገለጥ ነው፡፡ ስለሆነም ሃይማኖት እግዚአብሔር ራሱን ለእኛ ያሳየበት መንገድ፣ የሰው ልጅ ሊቀበለው በሚችለው መጠን ስለ ራሱ ማንነት ለእኛ የገለጠው እውነታ ነው፡፡

እግዚአብሔር አንድ ስለ ሆነ፣ ባሕርዩም የማይለወጥ ስለ ሆነ፣ ሃይማኖት (ይህ አምላክ ስለ ራሱ የገለጠው መግለጥ) አንድና የማይለዋወጥ ነው፡፡ ስለዚህም ሊኖር የሚችለው እውነተኛ ሃይማኖት አንድ ብቻ ነው፡፡ ብዙ ሃይማኖቶች አሉ ማለት ግን ወይ እግዚአብሔር በተለያየ ጊዜ የተለያየ ነገር ይናገራል ማለትን፣ አለዚያም ደግሞ ባሕርዩ ይለዋወጣል ማለትን ያስከትላል፤ ሆኖም እነዚህ አስተሳሰቦች ለእግዚአብሔር ሊነገሩ ቀርቶ ሊታሰቡ የማይገባቸው ጸያፎች ናቸው፤ እርሱ በተለያየ ጊዜ እርስ በእርሱ የሚቃረን የተለያየ ነገር አይኖርምና፣ ባሕርዩም አይለዋወጥምና፡፡ መለወጥ የፍጡር ባሕርይ እንጂ በእግዚአብሔር ዘንድ መለወጥ የለም፡፡ ስለዚህ ሃይማኖት አንድ ብቻ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ “አንድ ጌታ፣ አንድ ሃይማኖት፣ አንዲት ጥምቀት” የሚለው ለዚህ ነው፡፡ ኤፌ. 4፡5

ሃይማኖት፡- ተስፋ ማድረግ ሰው ከሞተ በኋላ በእግዚአብሔር በሕይወት እንደሚኖር ባለመጠራጠር ማመን ይህም ተስፋ መንግሥተ ሰማይ ነው፡፡ /፩ኛተሰ. ፬፥፲፬/ከትንሣኤ ድጓ ብንመለከት ሊቁ እንዲህ ይላል፡- «ተስፋ ሕይወት ተሠርዐ ፣ተስፋ ሕይወት ተሠርዐ፣ በሰማያት ተስፋ ሕይወት ተሠርዐ - የሕይወት ተስፋ ተሠራ፤ የሕይወት ተስፋ ተዘጋጀ፤ የሕይወት ተስፋ በሰማያት ተሠራ» ያለውን ማስረጃ እናገኛለን።

ሃይማኖት፡- ፍጡርና ፈጣሪ የሚገናኙበት ረቂቅ መንገድ ነው፡፡

1.2 እምነት

እምነት እግዚአብሔር የገለጠውን እውነት (ሃይማኖት) አዎ፣ እውነት ነው፣ ትክክል ነው ብሎ “አሜን” ብሎ መቀበል ነው፡፡ እግዚአብሔር የሚገልጠው እውነት (ሃይማኖት) በሰው መቀበል ወይም አለመቀበል ላይ የተመሠረተ አይደለም፤ ምን ጊዜም እውነት ነውና፡፡ “ባናምነው እርሱ የታመነ ሆኖ ይኖራል፤ ራሱን ሊክድ አይችልምና” እንዳለ፡፡ 1 ጢሞ. 2፡13 እንዲሁም “የማያምኑ ቢኖሩ አለማመናቸው የእግዚአብሔርን ታማኝነት ያስቀራልን?” እንደ ተባለ፡፡ ሮሜ 3፡3

ነገር ግን ይህን እግዚአብሔር ስለ ባሕርዩ፣ ስለ መግቦቱ በአጠቃላይ እኛ ልናውቀው የምንችለውን ያህል በአባታዊ ቸርነቱ የገለጠውን እውነት (ሃይማኖት) እውነት ነው ብለን ስንቀበለው እምነት ይሆናል፡፡ ይህ ማመንም ከእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ የሚያስገኝ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ይሆናል፡፡

--------- ------------ ------------ ------------ ------------------------------------------------------------ ------------ ------------ 2 ኛ
ገጽ ከ 33 ገጾች

ትምህርተ ሃይማኖት ርትዕት ፳፻
ዓ/ም

ለምሳሌ እግዚአብሔር ከአብርሃም ዘር በመወለድ በዕፅ የተረገመውን ዓለሙን (የሰውን ልጅ በሙሉ) በዕፀ መስቀል ላይ በመሰቀል ይባርከው ዘንድ ፈቃዱ ነበር፡፡ ይኸ የማይለወጥና የማይናወጽ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፡፡ እግዚአብሔር ይህን እውነት ለአብርሃም ሲገልጥለት፣ በዘጠና ዘጠኝ (99) ዓመቱ ልጅ እንደሚወልድና በእርሱ ዘርም አሕዛብ ሁሉ እንደሚባረኩ ሲነግረው ‘ሸምግያለሁ፣ ይህ እንዴት ይሆናል?’ ብሎ ሳይጠራጠር ስላመነ “አብርሃም አመነ፣ እምነቱም ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት” ተባለ፡፡ ዘፍ. 15፡3-6

እንዲሁም ይኽ እግዚአብሔር እርሱ ባወቀ በመለኮታዊ ምክሩ የወሰነው፣ አስቀድሞ ለአዳምና ለሔዋን ገና ከገነት ሲወጡ የሰጣቸው ተስፋ፣ ኋላም ለአብርሃም የነገረው ተስፋ ዘመኑ ደርሶ የሚፈጸምበት ጊዜ ሲደርስ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ወደ እመቤታችን ተልኮ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካላዊ ቃል በተለየ አካሉ ከእርሷ ሰው ሆኖ በግብረ መንፈስ ቅዱስ እንደሚወለድ ነገራት፡፡ ይኽ ማንም ሰው ሊለውጠው ወይም ሊያስተባብለው ወይም ሊያሻሽለው የማይችለው የእግዚአብሔር አምላካዊ ውሳኔ (ቁርጥ ሃሳብ) (ነገረ ሃይማኖት) ነው፡፡

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ይኽን ነገር ስትሰማ ነገሩ ከዚያ በፊት ያልተደረገ፣ ከዚያም በኋላ የማይሆን ስለ ሆነ ግራ ቢገባት
“እፎኑ ይከውነኒ ዝንቱ እንዘ ኢየአምር ብእሴ - ወንድ ሳላውቅ ይህ እንዴት ይሆንልኛል?” ብላ ጠየቀች፡፡ መልአኩም ሊያስረዳት ሞከረ፡፡ ነገር ግን ማስረዳቱ ብዙም የማያስኬድ ስለ ሆነበት “እስመ አልቦ ነገር ዘይሰአኖ ለእግዚአብሔር - ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና” ብሎ ዘጋ፡፡ እመቤታችንም ነገሩ የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነማ “ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ - አንተ እንዳልከው ይሁንልኝ፣ ይደረግልኝ” ብላ የእግዚአብሔር ቁርጥ ሃሳብና ፈቃድ እንደ ተነገራት በእርሷ እንዲፈጸም ይሁንልኝ ብላ በፍጹም እምነት ተቀበለች፡፡ ይህ በእምነት “ይኩነኒ” ብላ መቀበሏም እግዚአብሔር ቃል በማኅፀኗ በተዋሕዶ እንዲፀነሥ ምክንያት ሆኗል፡፡ የሔዋን እግዚአብሔርን አለማመን ከእግዚአብሔር መለየትንና ሞትን እንዳመጣብን የእመቤታችን ማመን ደግሞ እግዚአብሔር ባሕርያችንን ባሕርዩ አድርጎ ከእኛ ጋር እንዲሆን እና ሞትን የሚያስወግደው የሕይወት በር እንዲከፈትልን መነሻ ምክንያት ሆነን፡፡

በአንጻሩ ደግሞ ለጌታችን መንገድ ጠራጊ ይሆን ዘንድ መንፈቀ ዓመት ተቀድሞ የሚወለደው የመጥምቁ ዮሐንስን የመወለድ ነገር በተመለከተ መልአኩ ገብርኤል ካህን ለነበረው ለዘካርያስ “ዘካርያስ ሆይ፣ ጸሎትህ ተሰምቶልሃልና አትፍራ፣ ሚስትህ ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች፣ ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ …” ሲለው በእምነት አልተቀበለም፡፡ ሉቃ. 1፡13-17 ይልቁንም መልአኩን መልሶ “እኔ ሽማግሌ ነኝ፣ ሚስቴም በዕድሜዋ አርጅታለችና ይህን በምን አውቃለሁ?” አለው፡፡ 1፡18 በእምነት ከመቀበል ይልቅ ማረጋገጫ ምልክት ጠየቀ፡፡ በዚሀም ምክንያት ተግሣፅ ደረሰበት፡፡ እምነት እግዚአብሔር የሚሠራውን ሥራ፣ የገለጠውን እውነት እንደ ዘካርያስ ሳይጠራጠሩና ምልክት ሳይሹ እንደ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በአግባቡ ተረድቶ አሜን፣ ልክ ነው፣ ለይኩን ለይኩን ብሎ መቀበል ነው፡፡

በጸሎትና ነገረ ሃይማኖትን በሚናገሩ አንቀጾች መሀልም ሆነ መጨረሻ ላይ “አሜን” የሚለው ቃል የጸሎትና የእምነት መግለጫ ማሳረጊያ ሆኖ የሚነገረው ለዚህ ነው፡፡ ጸሎት ሲሆን ‘የተጸለየው ጸሎት ይሁንልን ይደረግልን’ ለማለት፣ የተነገረው ወይም የተነበበው ነገረ ሃይማኖት ሲሆን ደግሞ ‘አዎ፣ እኔም ይህንኑ አምናለሁ፣ የማምነው ይኸው ነው’ ለማለት ነው፡፡ ለምሳሌም ቅዱስ ጳውሎስ “ከእነርሱም (ከእስራኤላውያን) ክርስቶስ በሥጋ መጣ፣ እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው፤ አሜን” ይላል፡፡ ሮሜ 9፡5 አሜን ማለቱ ከዚያ በፊት የተናገረውን - ‘ክርስቶስ ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው’ - የሚለውን አዎን፣ እውነት ነው፣ የእኔም እምነት ይኸው ነው እንደ ማለት ነው፡፡

1.3 መታመን
መታመን ሲባል እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋና የተናገረው ቃል ለእኔም ይሆንልኛል፣ ይደረግልኛል፣ እርሱ ያድነኛል ይመግበኛል … ብሎ ሙሉ ተስፋንና ተአምኖን በእርሱ ላይ ማድረግ ነው፡፡ ቃሉ ከእምነት ጋር ተቀራራቢነት ያለው ቢሆንም በተለይ ግን በራሳችን ላይ የሚደርሱ ነገሮችን ለመቀበልና ለማሸነፍ

--------- ------------ ------------ ------------ ------------------------------------------------------------ ------------ ------------ 3 ኛ
ገጽ ከ 33 ገጾች

ትምህርተ ሃይማኖት ርትዕት ፳፻
ዓ/ም

በእግዚአብሔር ረዳትነትና አዳኝነት ላይ ያለንን የእምነት መጠን የሚገልጽ ነው፡፡ ለምሳሌም ሠለስቱ ደቂቅ በፊታቸው አስፈሪ የሆነ እሳት እየተንቀለቀለ እያዩ “የምናመልከው አምላካችን ከሚነደው ከእሳቱ እቶን ያድነን ዘንድ ይችላል፣ ከእጅህም ያድነናል፣ ንጉሥ ሆይ፣ እርሱ ባያድነን አማልክትህን እንዳናመልክ ላቆምከውም ለወርቁ ምስል እንዳንሰግድለት እወቅ” ብለው ወደ እሳቱ እስከ መግባት ደርሰው በእርሱ ታምነዋል፡፡ ዳን. 3፡16-18

“ባያድነን እንኳ” ማለታቸው አዳኝነቱን ወይም የሚያድን መሆኑን የመጠራጠር ሳይሆን አንደኛ የእግዚአብሔር ፈቃድ እነርሱ በሰማዕትነት ሞተው እንዲያከብሩት ይሁን ወይም ሌላ ስላላወቁ፣ ሁለተኛ ደግሞ በኃጢአታቸው ምክንያት ሳያድናቸው ቢቀር ያላዳናቸው እርሱ ማዳን ስለማይችል ሳይሆን በእነርሱ ለማዳኑ የበቁ አለ መሆን ምክንያት ስለሚሆን ነው፡፡ ሆኖም አረማዊው ንጉሥ ናቡከደነፆር ይህን ሁሉ ቢነግሩት ስለማይገባው “ባያድነን እንኳ” የሚል ጨመሩለት፤ ከእሳቱ ባያድናቸው አምላካቸውን እግዚአብሔርን ማዳን የማይችል አድርጎ እንዳይረዳ ለጥንቃቄ የተናገሩት ነገር ነው፡፡ ስለዚህ መታመን ሁለንተናችንን በእግዚአብሔር አዳኝነትና አባትነት ጥላ ሥር ማሳረፍ ነው፡፡

1.4 ሃይማኖት እንዴት ተገኘ?

“ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ፡፡” ይሁዳ 3
ሃይማኖት፡-

1) የተሰጠ፣ የተቀበልነው ነው፡፡

እግዚአብሔር ሃይማኖትን ሰጠ፣ እኛ ደግሞ ተቀበልን፡፡ የእኛ ድርሻ መቀበል ነው፡፡ የሰው ልጅ ሃይማኖትን ይቀበላል እንጂ ሃይማኖትን ሊሠራ ወይም ሊያሻሽል አይችልም፡፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ “የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቻቸዋለሁና፣ እነርሱም ተቀበሉት፡፡” በማለት የገለጸው ይህን ነው፡፡ ዮሐ. 17፡8

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ያመነውንና የያዘውን ሃይማኖት ከጌታ የተቀበለው መሆኑንና፣ ያን የተቀበለውንም በወንጌል ትምህርት እንዳወረሳቸው ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ሲያሳስባቸው እንዲህ በማለት ገልጾላቸዋል፡- “ወንድሞች ሆይ፣ የሰበክሁላችሁን፣ ደግሞም የተቀበላችሁትን፣ በእርሱም ደግሞ የቆማችሁበትን፣ በእርሱም ደግሞ የምትድኑበትን ወንጌል አሳስባችኋለሁ፤ … እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችሁ፡፡” 1 ቆሮ. 15፡1-3 እንዲሁም ስለ ምሥጢረ ቁርባን ባስተማረበት አንቀጽ ላይ “ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ደግሞ ከጌታ ተቀብያለሁና…” ብሏል፡፡ 1 ቆሮ. 11፡23

ወልድ ዋሕድ መድኃኒታችንም “ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደ ሆነ ይሉታል?” ብሎ ደቀ መዛሙርቱን ጠየቃቸው፡፡ እነርሱም፡- “አንዳንዱ መጥምቁ ዮሐንስ፣ ሌሎችም ኤልያስ፣ ሌሎችም ኤርምያስ፣ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ አሉት፡፡ እርሱም፡- እናንተስ እኔን ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ? አላቸው፡፡ ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ፡- አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ፡፡

ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፡- የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፣ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ፡፡ እኔም እልሃለሁ፣ አንተ ጴጥሮስ ነህ፣ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፣ የገሃነም ደጆች አይችሏትም፡፡” ማቴ. 16፡13-18

በሥጋና ደም አስተሳሰብ (በሰው ምርምርና ሐተታ) ሰዎች ስለ ጌታችን ሊሉት የሚችሉት ያን ጊዜ የነበሩት ሰዎች እንዳሉት ‘መጥምቁ ዮሐንስ፣ ወይም ኤልያስ ወይም ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ከማለት ያለፈ ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም ሰው ሆኖ እያዩት አምላክነቱን መረዳት በሥጋና በደም አስተሳሰብ ሊደረስበት የሚችል ምሥጢር አይደለምና፡፡ ጴጥሮስ ግን የወልድ ዋሕድ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰማያዊ አባቱ

--------- ------------ ------------ ------------ ------------------------------------------------------------ ------------ ------------ 4 ኛ
ገጽ ከ 33 ገጾች

ትምህርተ ሃይማኖት ርትዕት ፳፻
ዓ/ም

አብ የገለጠለትን ነገር - የኢየሱስ ክርስቶስን የአብ የባሕርይ ልጅነት - ስለ ተናገረ ጌታችን አመሰገነው፤ “ስምዖን ሆይ፣ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ” አለው፡፡

መቼም ቢሆን በሃይማኖት እግዚአብሔር የገለጠውን ትተን በራሳችን አስተሳሰብና በሚመስለን መንገድ እንሂድ ካልን ወደ እውነተኛው ሃይማኖት ልንደርስ አንችልም፡፡ በሐዋርያት ዘመን ከነበሩት ዓይነት ሰዎች የተሻለ ነገር ልንል አንችልም፡፡ ከዚያ ለመውጣትና ጴጥሮስ የመሰከረውን ለመያዝ ከሥጋና ከደም አስተሳሰብ መለየት የግድ ይላል፡፡ ጌታችን “ከዓለም ለሰጠኸኝ ሰዎች ስምህን ገለጥሁላቸው፡፡” ያለው ለዚህ ነው፤ ስሙንም፣ ማንነቱንም ሊገባን በሚችለው መጠን የገለጠልን ራሱ ነው እንጂ ሃይማኖት የሰው ልጅ በምርምር የደረሰበት ግኝት አይደለም፡፡ ዮሐ. 17፡6

ድጓ "ሃይማኖት እንተ እም ኀበ አብ ተፈጥረት፣ ኀበ ወልድ ታበጽሕ፣ኀበ መንፈስ ቅዱስ ትትፌጸም፡፡ይህ ማለት ሃይማኖት አብን ወላዲ /አባት/ ወልድን ተወላዲ/ልጅ/ መንፈስ ቅዱስን ሠራጺ በማለት ትጀመራለች፤ ትፈጸማለች፡፡ አብን ወላዲ አስራጺ ሳይሉ ወልድን ተወላዲ መንፈስ ቅዱስን ሰራጺ ማለት አይቻልም፡፡ አብን በልብነት መቀበል ወልድን በቃልነት መንፈስ ቅዱስን በሕይዋትነት /በእስትንፋስነት/ አምኖ መቀበል ነውና እንተ እምኀበ አብ ተፈጥረት አለ ሊቁ ተገኘች ማለቱ ሃይማኖት የተገኘችው ከእግዚአብሔር ነውና፣ ሃይማኖት ከአብ ተፈጠረች፤ወደ ወልድ ታደርሳለች፤ በመንፈስ ቅዱስም ትፈጸማለች፡፡ "የሚል ቃል እናገኛለን ፡፡ስለዚህ ሃይማኖት የሰው ልጆች ከዕውቀት ማነስ ከፍርሀትና ከድንጋጤ ያመጡት አይደለም፡፡

ድጓ በከመ ይቤ እግዚእነ በወንጌል ኵሉ ዘየዐቅብ ቃልየ ይመስል ብእሴ ጠቢበ ዘሐነጸ ቤቶ ዲበ ኰኵሕ ነፍኁ ነፋሳት፣ ዘንሙ ዝናማት ፣ ወውኅዙ አፍላጋት ፣ ወገፍዕዎ ለውእቱ ቤት ፣ ወ ኢወድቀ ፣ እስመ ዲበ ኰኵሕ ተሣረረ፡፡ = ጌታችን በወንጌል እንዳለው ቃሌን የሚጠብቅ ሁሉ ቤቱን በዐለት ላይ የሠራ ጥበበኛ ሰውን ይመስላል፤ ነፋሳት ነፈሱ፣ ዝናምም ዘነመ ፣ ወንዞችም ፈሰሱ ፣ ይህን ቤት ገፉት፤ አልወደቀም፡፡ በዐለት ላይ ተሠርቷልና ” ይላል።

2. የሃይማኖትና የእምነት ጥቅም

ሃይማኖት፡- ጥበብ ናትና ወደ ብቃት ታደርሳለች። /ምሳ. ፱፥፩-፯፣ ማቴ. ፳፪፥፩-፲፪፣ ፪ኛ ጢሞ . ፫፥፲፬-፲፯/ ድጓም እንዲህ ይላል ጥበብ ሐፀነተከ ከመ ጥ በ ልቡና ረሰየተከ መካና አእምሮ ታጌብረከ ለምህሮ ወንጌለ መለኮት ሰበከ ስምዐ ጽድቅ ኮንከ - ጥበብ እንደ ጡት አሳደገችህ፣ ልቡና ቦታዋ አደረገችህ አእምሮም ለማስተማር ታበቃሀለች፣ ስለዚህ የመለኮት ወንጌልን ሰበክህ፣ የጽድቅም ምስክር ሆንህ» በማለት ያመሰጥራል።

ሃይማኖት

• ተስፋ ለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ የማናየውን ነገር የሚያስረዳ ነው፡፡ /ዕብ. ፲፩፥፩/

• ኃይልና ሥልጣን ትሰጣለች። /ማር. ፲፮፥፲፮-፲፱ ፣ ማቴ . ፲፥፰/

--------- ------------ ------------ ------------ ------------------------------------------------------------ ------------ ------------ 5 ኛ ገጽ ከ 33 ገጾች

ትምህርተ ሃይማኖት ርትዕት ፳፻
ዓ/ም

የሐዋርያት ድጓ "አብሖሙ ይኪዱ ዲበ ኲሉ ኀይለ ጸላኢ፤ ወይቤሎሙ ወሀብኩክሙ ሥልጣነ፤ ዱያነ ፈውሱ፤ ዐቢይ ኀይል ወተአምር ይትገበር በእደዊሆሙ ለሐዋርያት ይቤሎሙ ኢየሱስ ለአርደኢሁ አጋንንተ አውጽኡ፤ እለ ለምጽ አንጽሑ፤ ጸጋ ነሢአክሙ በጸጋ ሀቡ … - በእባቡ፣ በጊንጡ /በጠላት ኀይል ሁሉ / ላይ ይረግጡ ዘንድ ድውያንን ትፈውሱ ዘንድ ሥልጣን ሰጠኋችሁ አላቸው ታላቅ ተአምር ታላቅ ኀይል በሐዋርያት እጅ ይደረጋል ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ አላቸው አጋንንትን አውጡ ፣ ድውያንን ፈውሱ ፣ ለምጻሙን አንጹ ፣ ያለዋጋ … የተቀበላችሁትን ያለዋጋ ስጡ ”የሚል ማብራሪያ ይሰጠናል፡፡

• ሰው ከኃጢአት ከሰይጣን ግዞት ነጻ የሚሆንበት ነው፡፡ ሮሜ. ፮÷፳፪፣፩ኛጴጥ. ፭÷፰፣፩ኛዮሐ. ፬÷፩-፮፣ያዕ. ፬÷፯

• በኃጢአት ምክንያት ከሚመጣ ቅጣት ይሰውራል። /ዘፍ. ፮፣ዘፍ. ፱፣ዕብ. ፲፩÷፯/

• የጽድቅና የበረከት መገኛ ነው። /ዘፍ. ፲፪÷፩-፰፣ዕብ. ፲፩÷፰/

ድጓ ከአብርሃም፡- “ወጽአ አብርሃም እምድረ ካራን፣ ወቦአ ብሔረ ከነዓን፣ ተአመነ አብርሃም በእግዚአብሔር እንበይነዝ ጽድቀ ኮኖ - አብርሃም ከካራን ምድር ወጣ፣ ወደ ከነዓን አገር ገባ፣ በእግዚአብሔርም ታመነ፣ ስለዚህ ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት፡፡”

• ለሰማዕትነት ያበቃል፡፡ዳን.፮፣ዕብ. ፲፩÷፴፪-፵፣የሐዋ. ፮÷፰-፲፭፣፯÷፩-፷፣ማቴ. ፲÷፳፰፣ሉቃ. ፲፪÷፬-፭.ዳን.፫÷፲፭

ድጓ ዘሠለስቱ ደቂቅ፡- “ይቤሎሙ ንጉሥ እምከመ ሰማዕክሙ ቃለ ቀርን ወዕንዚራ ስግዱ ለምስል ዘወርቅ ዘገበርኩ፡፡= ንጉሡም እንዲህ አላቸው፡፡ የመለከቱንና የእንቢልታውን ድምፅ በሰማችሁ ጊዜ ለሠራሁት ምስል ወድቃችሁ ብትሰግዱ መልካም ነው፡፡”አላቸው።

ድጓ ዘሠለስቱ ደቂቅ “ከመ ታእምር ንጉሥ አምላከከሂ ኢናመልክ አምላከነሂ ናመልክ ለምስል ዘወርቅ ዘገበርከ ኢንሰግድ ለከ፡፡= ንጉሥ ሆይ ታውቅ ዘንድ እንወዳለን ፤አምላክህንም አናመልክም፤ አምላካችንን እናመልካለን እንጂ፤ ላቆምከው ለወርቅ ምስል አንሰግድም አሉ፡፡”

• ድንቅ ተአምራትን ማድረግ ያስችላል። /ዮሐ. ፲፬÷፲፪/ ለሚያምን ሁሉ ይቻላልና/ ማር. ፱÷፳፫/ በእርሱ በማመናቸው ሙት
ያስነሡ፣ በጥላቸው ፣በልብሳቸው ሳይቀር ድውይ ይፈውሱ በርካታ ገቢረ ተአምራት ያደርጉ ነበር፡፡/ የሐዋ.፫÷፩-፲፣፱÷ ፴፪፣፲፮÷፲፮-፲፰፣ የሐ.፭÷፲፪፣፭÷፲፭ ፣፲፱÷፲፩

የሃይማኖት አስፈላጊነትም ጠቅለል ባለ መልኩ፡ -
ለሰው ሁለንተና ሕይወት ሃይማኖት በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡ በአጠቃላይ የሕይወት ምንጭ ከሆነው ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር የሚያስችለው ሃይማኖት ነው፡፡ ሃይማኖት የሌለው ሰው ከሕይወት የተለየ ምውት ነው፡፡ በሃይማት የጸጋ ልጅነትን፣ ከእግዚአብሔር ጋር መኖርን፣ርስቱን መውረስን ወዘተ ያስገኛል። በዚህ ዓለም ሕይወትም መረጋጋትን፣ ተስፋን፣ ሰላምን፣ አርቆ ማሰብን፣ከሱስ መጠበቅን፣ በረከት ረድኤትን ያስገኛል። ለሀገርም በማኅበረ ሰብእ ውስጥ መተማመንን፣ በሥራ ትጋትን፣ ፍትሕ አክባሪነትን ወዘተ ያበረክታል።

3. የእምነት መመሪያዎች/መሠረተ ሃይማኖት/

1. ዶክትሪን (ዶግማ)

--------- ------------ ------------ ------------ ------------------------------------------------------------ ------------ ------------ 6 ኛ ገጽ ከ 33 ገጾች

ትምህርተ ሃይማኖት ርትዕት ፳፻
ዓ/ም

ዶግማ ቃሉ የጽርዕ ሲሆን መሠረታዊ የሃይማኖት አስተምህሮ ማለት ነው፡፡ ይህም መሠረታዊ የሆነው እግዚአብሔር የገለጠው እውነት ሲሆን አስቀድሞ በሕግና በነቢያት ያናገረው፣ ኋላም እርሱ ራሱ ሰው ሆኖ ያስተማረውና ቅዱሳን ሐዋርያት የጻፉልንና ያስተማሩነረ እውነት ነው፡፡ ለምሳሌም ዶክትሪን (ዶግማ) ከሚባሉት መካከል፡- ምስጢረ ሥላሴ፣ ምስጢረ ሥጋዌ፣ ምስጢረ ጥምቀት፣ ምስጢረ ቁርባን፣ ምስጢረ ትንሣኤ ሙታን፣ የእመቤታችን ወለዲተ አምላክነትና የቅዱሳን አማላጅነት ወዘተ ናቸው፡፡

2. ቀኖና

ቀኖና ቃሉ የጽርዕ ሲሆን ትርጉሙም ሕግ፣ሥርዓት፣ደንብ፣ፍርድ፣ቅጣት፣መጠን፣ልክና መለኪ ያ መለት ነው፡፡

የቀኖና ቤተ ክርስቲያን ምንጮች

1.መጽሐፍ ቅዱስ - መጽሐፍ ቅዱስ የቀኖናተ ቤተ ክርስቲያን ዋና መሠረት ነው፣ በውስጡም ብዙ ቀኖናት አሉ፡፡ ለምሳሌ ስለ ጾም፣ ስለ ጸሎት፣ ስለ ምጽዋት፣ (ማቴ. 6፡ 1-18) ስለ ምሥጢረ ቁርባን አፈጻጸም (1 ቆሮ. 11፡16-34)፣ ስለ ወንዶችና ሴቶች አለባበስና ጸጉር አቆራረጥ ( 1 ቆሮ. 11፡1-15) ወዘተ

2. የሐዋርያት ሲኖዶስ፡-

ቀኖናተ ሐዋርያት እየተባሉ የሚጠሩ ሁለት መጻሕፍት አሉ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፡-

• ሲኖዶስና
• ዲዲስቅልያ ናቸው፡፡
3.ዓለም አቀፍ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤያት

• ጉባኤ ኒቂያ
• ጉባኤ ቁስጥንጥንያ
• ጉባኤ ኤፌሶን ናቸው
የቀኖና ጠቀሜታ

• መናፍቃንና ኑፋቄ ይለይበታል
• የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መልክ እንዲኖረው ያደርጋል
• የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ይጠብቃል፣ በሁሉም ቦታ ተመሳሳይ የሆነ አገልግሎትና ሥርዐት እንዲኖር ያግዛል ዮሐ 15፡1-29
• በአጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን የሆነውን የቤተ ክርስቲያን ካልሆነው መለያ፣መለኪያ በመሆን ያገለግላል

ቀኖናትን ማን ይወስናል ?

--------- ------------ ------------ ------------ ------------------------------------------------------------ ------------ ------------ 7 ኛ ገጽ ከ 33 ገጾች

ትምህርተ ሃይማኖት ርትዕት ፳፻
ዓ/ም

አንድ ሰው በዘፈቀደ ተነሥቶ ቀኖናትን መወሰን ወይም ማሻሻል አይችልም፡፡ ቀኖና በባሕርይው ሊሻሻል፣ ሊለወጥ የሚችል ነገር ነው፡፡

ይሁን አንጂ መወሰኑም ሆነ ማሻሻሉ የሚፈጸመው በሐዋርያት እግር በተተኩ በጳጳሳት ጉባኤ (በቅዱስ ሲኖዶስ) ነው፡፡ ይህንንም ስንናገር ከእግዚአብሔር የተቀበልነውን ነው እንጂ በልብ ወለድ አይደለም፡፡ ሥርዐትን የሠራ ራሱ እግዚአብሔር ነው፡፡ ሥርዐትን አስተማሪ ራሱ ፈጣሪያችን ነው፡፡መዝ. ፩፻፲፰÷፳፬፣፸፩

3.ትውፊት

ትውፊት አወፈየ ሰጠ ከሚለው የግእዝ ቃል ወጣ ሲሆን ትርጉሙም፡- ቅብብል፣ ርክክብ ማለት ነው፡፡

ትውፊትና ቤተ ክርስቲያን

ቤተ ክርስቲያናችን በክርስቲያናዊ ትውፊት ታላቅ ቦታ ትሰጣለች፡፡ ጥንታዊት በመሆንዋ ከቀደምት አበው የወረሰችው አያሌ ነገር አሏት ፤ እነርሱም ሁለት ዓይነት ናቸው፡፡

1. ቁሳውያን፡- መጻሕፍት ፣ ንዋየ ቅድሳት ፣ አብያተ ክርስቲያናት ፣ ገዳማትና አድባራት ወዘተ የዚህ ክፍል ናቸው፡፡
2. ቃላውያንና ራእያውያን፡- ትውልዱ ከአባቶቹ በመስማት ፣ በማየት ለኑሮው የሚጠቀምባቸው ነገሮች ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- ባሕሉ ንግግሩ እና ሥርዐቱ ከአባቶቹ አይቶና እየሰማ የሚቀበላቸው ናቸው፡፡

ትውፊትና ቅዱሳት መጻሕፍት

የቤ/ክ አስተምህሮ ከሁለት ምንጮች የተገኙ ናቸው፡- ቅዱሳት መጻሕፍት እና ቅዱስ ትውፊት (Sacred Tradition) ናቸው፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት የተገኙበት ዐውድ እንዲሁም የሚተረጎሙበትና የምንረዳበት ዐውድና መሠረት ቅዱስ ትውፊት ነው፡፡ ትውፊት ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር የሚጋጭ የሚመስላቸው ሰዎች አሉ፡፡ ነገር ግን ደም ከደም ጋር እንደማይጋጨው ሁሉ እነርሱም አይጋጩም፡፡ ምክንያቱም ትውፊት መጽሐፍ ቅዱስን ያገኘንበት መንገድ ነው፡፡ አበው መጽሐፍ ቅዱስ ይህ ነው ብለው ባያስረክቡን ኑሮ ከየት ይመጣ ነበር? ይህ ትውልድ በምን ያውቀው ነበር? ለማግኝት የቻልነው አበው ስላቆዩልን ቤተ ክርስቲያንም ስላረጋገጠችልን አይደለምን? ትውፊት የቅዱሳት መጻሕፍት ቃል እንዳይፋለስ ይጠብቃል፡፡ አበው መጻሕፍትን ሲያስረክቡን የደራሲውን ገድል፣ የተጻፈበትን ባህል፣ የመጽሐፍቱን ትርጓሜ ከምንጩ የቀዱትን ጭምር ነው፡፡ ይህም ማንም በየትም ዘመን ተነሥቶ የራሱን ሃሣብና ፍልስፍና በመጨመር የቅዱሳት መጻሕፍትን ቃል እንዳያጣምም አድርጐታል፡፡ በትውፊት የመጡልን ብዙ ትምህርቶች አሉ፤ ሆኖም የትውፊት መመዘኛውና መለኪያው በመጽሐፍ ቅዱስ ያለው ትምህርት ነው፤ “ኢትጻኡ እም ቃለ መጻሕፍት - ከተጻፈው አትለፉ” ተብሏልና፡፡ 1 ቆሮ. 4፡6

--------- ------------ ------------ ------------ ------------------------------------------------------------ ------------ ------------ 8 ኛ
ገጽ ከ 33 ገጾች

ትምህርተ ሃይማኖት ርትዕት ፳፻
ዓ/ም

ክፍል ሁለት

ትምህርተ እግዚአብሔር

እግዚአብሔር የማይመረመር ረቂቅ በዚህ ጊዜ ተገኘ የማይሉት ቀዳማዊ በዚህ ጊዜ ያልፋል የማይሉት ደኃራዊ ይህን ዓለም ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ የፈጠረ ዳግመኛም ዓለምን ከመኖር ወደ አለመኖር አሳልፎ የሚኖር ኃያል ፈጥሮ የሚገዛ ጌታ ነው፡፡

ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ማወቅ እንችላለን?

• “በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? እንዲሁም ደግሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር
ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም፡፡” 1 ቆሮ. 2፡11-12
• “ከአብ በቀር ወልድን የሚያውቅ የለም፣ ከወልድም በቀር፣ ወልድም ሊገለጥለት ከሚፈቅድ በቀር አብን የሚያውቅ የለም፡፡” ማቴ. 11፡27
• “በፈጣሪና በፍጡር መካከል መጨረሻ የሌለው ሸለቆ (ጥልቀት) አለ፡፡” ቅ. ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ
• “በፈጣሪና በፍጡር መካከል ማንም ሊያልፈው የማይችለው ክፍተት አለ፡፡” ቅ. ኤፍሬም ሶርያዊ

ቅዳሴ ኤጲፋንዮስ፡- “ቀዳማዊ ውእቱ ዘኢይብልዎ እማእዜ ወማእከላዊ ውእቱ ዘኢይብልዎ እስከ ይእዜ ወደኃራዊ ውእቱ ዘኢይብልዎ እስከ ዝየ = ከመቸ ወዲህ የማይሉት ቀዳማዊ እስከ ዛሬ ” የማይሉት ማእከላዊ እስከዚህ የማይሉት ደኃራዊ ነው፡፡

ቅዳሴ ጎርጎርዮስ፡- “አልቦ ጥንት ለህላዌሁ ወአልቦ ማኅለቅት ለክዋኔሁ - ለአኗኗሩ ጥንት የለውም ለአኳኋኑም ፍጻሜ የለውም፡፡ ”

ሰውን ጻድቅ ቢሉት ሐሰት ሀብታም ቢሉት ድኽነት ኃያል ቢሉት ድካም ይስማማዋል። እሱ ግን ሐሰት የሌለበት ጻድቅድኽነት የሌለበት ባለጸጋ ድካም የሌለበት ኃያል ነው፡፡ መዝ ፯ ÷፲፩

የእግዚአብሔር መኖር በምን ይታወቃል?

1. በሥነ ፍጥረት ሮሜ. ፩÷፳፣ኢዮ.፲፪÷፯፣ ዕብ.፲፩÷፫፣ መዝ. ፲፰÷፩
2. በኅሊና ምስክርነት ሮሜ.፪÷፲፬
3. በመግቦቱ መዝ. ፩፻፫÷፳፯፣ ፩፻፴፭÷፳፭፣፩፻፵፬÷፲፭/

በተጨማሪም ድጓ “ዐይነ ኲሉ ነፍስ ይሴፎ ኪያሁ ይሁቦሙ ሲሳዮሙ በጊዜሁ” የሰው ሁሉ ዐይን እርሱን ተስፋ ያደርጋል ፤እርሱም ምግባቸውን በየጊዜው ይሰጣቸዋል በማለት ያስረዳናል፡፡
4. በቃለ እግዚአብሔርና በታሪክ ምስክርነት መዝ. ፹፮÷፮፣አሞ. ፫÷፯፣ዕብ. ፩÷፩-፫…
5. በአካላዊ ቃል በኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ መገለጥ - ይህ ራሱ እግዚአብሔር ሰው ሆኖ ስ ራሱ የነገረን ፍጹም መገለጥ ነው፡፡

--------- ------------ ------------ ------------ ------------------------------------------------------------ ------------ ------------ 9 ኛ ገጽ ከ 33 ገጾች

ትምህርተ ሃይማኖት ርትዕት ፳፻
ዓ/ም

2. የእግዚአብሔር ስሞችና ትርጓሜያቸው

ስም፡- አንድ ነገር የሚጠራበት የሚታወቅበት ማለት ነው፡፡
በግልጽ ከሚታወቁት ስመ እግዚአብሔር ሌሎቹ ስሞቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡
ያህዌ ፦ ያለና የሚኖር፣ አዶናይ ፦ ጌታ፣ ኤልሻዳይ ፦ ሁሉን ቻይ፣ ኤል ፦ ኀያል አምላክና ሌሎችም
ሚል.፪÷፪፣ሕዝ ፴፱÷፪፣መዝ. ፩፻፴፬÷፩፫ ፣ፊል.፪÷፲

እግዚአብሔር የሚታወቅባቸው (መገለጫዎቹ የሆኑ) ስሞች

በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር ህልውና ስናምን የማይታይና የማይመረመር ከመሆኑ የተነሣ ስለ እርሱ ፍጹም ዕውቀት ሊኖረን አልቻለም፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር እረቂቅ አምላክ ነውና፡፡ የሚመለከውም በመንፈስ ነው፡፡ ዮሐ 424 እግዚአብሔር አምላክ አኗኗሩ ምጡቅ ባሕርዩ ረቂቅ ከመሆኑ የተነሣ ለምርምራችን በር አይሰጠንም እግዚአብሔር ያለና የሚኖር እንጂ የተፈጠረ አይደለምና ስለዚህ ከፍጥረት አስተሳሰብ ውጭ ስለሆነ ሊታይና ሊመረመር አይችልም፡፡

ቅዱሳት መጻሕፍት በገለጡልንና ራሱ አምላካችን በቸርነቱ ከሰው ልጅ ጋር በአደረገው ግንኙነት መሠረት እርሱ የማይታወቅና ረቂቅ የሆነው ባሕርዩ ከሚገለጥባቸው መገለጫ የሆኑ ቃላት መካከል የሚከተሉትን እንመለከታለን፡፡

1. ዘለዓለማዊነት፡- ራእ 48፤
2. ምሉእ በኩለሄ - በዓለሙ ሙሉ መሆኑ፡ - መዝ 1398-10
3. ከሃሌ ኩሉ መሆኑ፡ - 1827 ኢዮ 422
4. የእግዚአብሔር ፍጹም ጥበበኛነት፡ - ሮሜ 1133 በአጭሩ እነዚህ ተገለጹ እንጂ የእግዚአብሔር የባሕርይ መገለጫዎች በሰው አእምሮ ተሰፍረውና ተቆጥረው የሚቀመጡ አይደለም፡፡ ነገር ግን አባቶች በመጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስ የገለጸላቸውን ስለጻፉልን ሌሎችን የባሕርዩ መገለጫዎች የሆኑትን መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብና በመጠየቅ እንረዳ፡፡

ክፍል ሦስት

ትምህርተ አዕማደ ምስጢር
የ U ስ Ö=` ትርጉም

ሀ . UeÖ=`:- #›S ስ Ö[/ሰ Ö[/$ U ስ Ö=` ›Å[Ñ'c¨[' Åuk'›[kk'ŸT>K¨< ¾Ó እ´ Óe ¾}Ñ– nM c=J” Éwp' ሥ¨<`' iiÓ የሆነ /’Ñ` Ndw“ U¡`/ TKƒ ’¨<:: eK ዚ IU UeÖ=` TKƒ ›UL"©

--------- ------------ ------------ ------------ ------------------------------------------------------------ ------------ ------------ 10 ኛ ገጽ ከ 33 ገጾች

Ów`' S”ðd©፣ [mp' ¾TÃቃÃ፣ ¾TÃቃ¨p' ¾TÃቃS”፣ ¾T>Å’p w‰ TKƒ ’¨<:: Ã¤¨<U uYÒ ወÃ” ¾TÃቃÃ፤ ’Ñ` Ó” uእU’ƒ ወÃ” ¾T>ቃÃ TKƒ ’¨<:: ›”ÉU uእÓ²=›wN?` ðnÉ“ †`’ƒእ”Í= ¾c¨< MÏ u^c< Øuw S`Ua K=Å`eufl“ K=Á¨<k¨< ¾TÃ‹M TKƒ ’¨<::

UeÖ=`፡- ¾õÖ<^”“ ¾ð×] UeÖ=` }wKA uG<Kƒ K=ŸðM Ã‹LM::

- ¾õÖ<` UeÖ=`:- Ã¤U ¾SLእ¡ƒ UeÖ=`“ ¾c‹ UeÖ=` uSvM Ãቃወቃል።

1. ¾SLእ¡ƒ UeÖ=`:- c¨< eK SLእ¡ƒ ¾T>Á¨<k¨< እÓ²=›wN?` ¨Ê“ ðpÊ upÆdƒ SéQõƒ ¾ÑKçKƒ” ÁIM w‰ ’¨<:: °´.c<~.ፏ፥ፘፘ-ፘፗ

2. ¾c‹ UeÖ=`:- c‹ uMu<“†¨< ѡ¨<[¨< ¾T>Ã²<ƒ ¨ÃU G<Kƒ“ ŸG<Kƒ uLÃ uJ’< c‹ S"ŸM KÑ>²?¨< uÉwp uሥ¨<` ¾T>Á´ c=J” uሐÅƒ uÑ>²? ¾T>ðቃ ¾T>ÑKØ ¾T>ቃ¨p ’¨<:: /T,.፲፥ፘፘ/

3. ¾ð×] UeÖ=` :- Ÿc¨< ጎK=“ uLÃ eKJ’ ÁK እÓ²=›wN?` ðnÉ ¾TÃÑKØ ’¨<:: ¾c¨< ›እUa ›ex“ S`Ua ¾TÃÅ[euƒ [mp eKJ’ ¾›UL¡ IM¨<“ ¾›UL¡ Ów` ¾›UL¡ UeÖ=` ÃvLM:: u}KÃU uYÒ© U`U` uØuw YÒ© S[Çƒ ¾TÃ‰M eKJ’ ነው። ፭ qa.ፏ:፲፱

***K. ›°TÉ:-*** #®UÉ$ nM’~ ¾Óእ´ s”s c=J” u›T`— Ó” G<Kƒ ወÃ’ƒ ƒ`ÕT@ ›K¨<:: Ã¤¨<U Ku?ƒ c=J” Ucf ÃvLM:: ›°TÉ TKƒ ÅÓV Ucf‹ TKƒ ’¨<:: KêQðƒ c=J” dÃK¨Ø u^c< ®UÉ }wKA ÃÖ^M:: G<’@ቃ¨<U ¾Ñê eófS¡ðÁ“ SSÖ— eKJ’ Ucf ŸTKƒ ¾^k ›ÃÅKU::

u?ƒ ÁK ®UÉ /Ucf/ እ”ÅTÃqU እ”ÅTÃç“ G<K< u?}¡`e+Á”U ÁK እUe~ ›°TÅ UeÖ=` ሀM¨<“ ¾LƒU:: K²=IU ’¨< pÆe ä¨<KAe /፭— qa.፲፱፥፲፱/ us”s ŸT>’Ñ` w²< nM ÃMp uu?} ¡`e+Á” ›Uefl nLƒ” M“Ñ` እሻለሁ ያለው።

እUe~ ›°TÅ UeÖ=` ¾}vሉƒU:-

1. ም e ጠረ YLc?'
2. ም e ጠረ YÒ«'
3. ም e ጠረ ØUkƒ'
4. ም e ጠረ l`v”

ትምህርተ ሃይማኖት ርትዕት ፳፻
ዓ/ም

5. ም e ጢረ ƒ”X›? S<ታ” “†¨<

1. ም Y ጢረ ሥላሴ

1.1 ሥላሴ ማለት ምን ማለት ነው ?

YLc?:- ¾T>K¨< nM #WKc$ Zeƒ ›Å[Ñ ŸT>K¨< ¾Ó እ´ Óe ¾}Ñ–
c=J”፡ õˆ¨<U ልዩ Zeƒ ነት TKƒ ’¨<:: u›ÖnLÃ ም e ጢረ YLc? TKƒ ¾ እ Ó²=›wN?` አንድነትና M¿ Zeƒ’ƒ
ም e ጢር TKƒ ’¨<::
1.2 “ቅዱስ እግዚአብሔር ቅድስት ሥላሴ ብለን በተለያየ አንቀጽ ለምን እንጠራለን ” “ ” ?

በሴት አንቀጽ መጥራታችን እ Ó²=›wN?` እ”Å እ“ƒ `ኅ\ኅእ”ÅJ’ KSÓKê ’¨<:: እ”Ç=G<U ›”É’~” KSÓKê
pÆe እ Ó²=›wN?` እ”LK”:: u¨”É ›”kê pÆe TK ታ‹” እ”Å ›vƒ Ã”ŸvŸu“M ÁewM“M ና ’ው::
¾ እ Ó²=›wN?` ›”É’ƒ“ Zeƒ’ƒ M¿ ¾}vKuƒ U¡”Áƒ ŸõÖ<^” ¨<eØ uv ሕ`Ã ›”É፤ u›"M Zeƒ ¾J’ õÖ<` eKTÃÑ˜ ’¨<::

#እ”Ç=I እ“U“K” እ”Ç=IU እ”ታ S“K”። አንድነት ከሦስትነት ፈጽሞ እንዳይለይ አንድነትን ከሦስትነት በባሕርይ ሳንለይ

ሦትነትን እናምናለን፡፡ ሦስትነት ካንድነት በባሕርይ ፈጽሞ እንዳይለይ፤ ሦስትነትን ከአንድነት በባሕርይ ሳንለይ አንድነትን እናምናለን፡፡ አብርሃም ከይስሐቅ እንዲበልጥ እንዲቀድም አብ ከልጁ የሚበልጥ የሚቀድም አይደለም፡፡ ይስሐቅ ከያዕቆብ እንዲቀድም እንዲበልጥ ወልድ ከመንፈስ ቅዱስ የሚበልጥ የሚቀድም አይደለም፡፡ ያዕቆብ ከይስሐቅ እንዲያንስ ወደኋላ እንዲሆን መንፈስ ቅዱስም ከወልድ አያንስም ወደኋላ አይሆንም፡፡ይስሐቅም ከአብርሃም እንዲያንስ ወደኋላ እንዲል ወልድም ከአብ ወደኋላ አይሆንም አያንስም፡፡ አብርሃም ይስሐቅን በአባትነት ሥራ እንዲያዘው ይስሐቅም ያዕቆብን እንዲያዘው አብ አባት ነኝና ብሎ ወልድን አያዝዘው ወልድም ልጅ ነኝ ብሎ አልታዘዝም

አይልም፡፡ ይስሐቅም ያዕቆብን እንዲያዝዘው ወልድ መንፈስ ቅዱስን አያዝዘውም፡፡ እንደ አብርሃምና እ”Å ÃeNp እ”Å Á°qw
Zeƒ የምንል አይደለም uvQ`Ã ›”É ’¨< እ”Í=:: ŸõØ[ƒ G<K< እ”ÅT>kÉU እ”Å ›ÇU ›”É ¾U”M ›ÃÅKU:: uv ሕ`Ã ›”É c=J” Zeƒ ’¨< እ”LK” እ”Í=$ ›v ሕ`Áqe pÇc? T`ÁU l. ፷፰

ይህ የም e ጢረ ሥላሴ ትምህርት ስለምን ያስረዳል ? eK እ Ó²=›wN?` ›”É’ƒ“ Zeƒ’ƒ

1. የእግዚአብሔር ›”É’ƒ Zeƒ’ƒ uU” uU”É” ’¨<;
 u ስም' በ›"M'uÓw`'
2. የሥሉስ ቅዱስ አንድነት ወይም የእግዘአብሔር አንድነት በምንድን ነው?

 በ v ሕ`Ã'uIM¨<“'uðnÉ'uSK¢ƒ፣ በርቀት፣ በምልዐት. . . ’¨<::

ስለ እግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት በመጽሐፍ ቅዱስ

²õ.፩፥፳፮/። አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ በሰዓታቱ፡- pÆe pÆe pÆe እ Ó²=›wN?` ²Ñwa K›ÇU u²²=›G< ›`›Á ¨›UdM ›ÇU” u እ`c< ›`›Á“ u እ`c< ›UdM ¾ðÖ[¨< እ Ó²=›wN?` UeÒ“ ÃÑvªM! UeÒ“ ÃÑvªM! UeÒ“ ÃÑvªM! ወይም ልዩ ንጹሕ፣ ክቡር ነው፡፡ ይላል /²õ.፪፥፲፰/ /²õ.፫፥፳፪/ /²õ.፲፩፥፩/ ²õ ፲፰ S´.፴፪፥፭……………..

--------- ------------ ------------ ------------ ------------------------------------------------------------ ------------ ------------ 12 ኛ
ገጽ ከ 33 ገጾች

ትምህርተ ሃይማኖት ርትዕት ፳፻
ዓ/ም

የም e ጢረ ሥላሴ ትምህርት ምሳሌዎች
የእግዚአብሔር ባሕርይ የማይመረመርና ሊደረስበት የማይቻል ምጡቅና ረቂቅ መሆኑን፣ ከሰዎችና ከመላእክት አእምሮ የራቀና የተሰወረ
መሆኑን አይተናል፡፡ ስለሆነም ለእግዚአብሔር ተስማሚና ተገቢ የሆነ ምሳሌ የለም፣ ሊኖርም አይችልም፡፡ ብዙ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት
አባችም ለእግዚአብሔር ምሳሌ መመሰልን አይደግፉትም፡፡ ሆኖም ምናልባት ለአእምሯችን መረዳት የተሻለ ይረዱንና ያግዙን ከሆነ በማለት የሚከተሉት ምሳሌዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ምሳሌዎች ለእኛ መረዳት ይረዱን እንደሆነ በማለት የቀረቡ ናቸው እንጂ እግዚአብሔርን ሙሉ
በሙሉ ይወክላሉ ወይም ይገልጻሉ ማለት እንዳልሆነ ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል፡፡

1. በመጀመሪያ በምሳሌነት የምጠቅስላችሁ መንፈሳዊት የኾነችውን የእያንዳንዳችንን ነፍስ ነው፡፡ ለዚች ነፍሳችን ሦስት ነገሮች እንዳሏት አውቀናል፡፡ እነዚህም ለባዊነት፣ ማለትም ክፉና ደጉን ለይቶ የማወቅ ሥልጣን፣ ነባቢነት፣ ማለትም ስሜትን በንግግርና በተለያየ ድርጊት የመግለጽ ችሎታ ሥልጣን፣ ሕያውነት፣ ማለትም ሳትሞት ለዘለዓለም መኖር ናቸው፡፡ በነፍስ ለባዊነት እግዚአብሔር አብ ይመሰላል፡፡፡በነባቢነቷ እግዚአብሔር ወልድ ይመሰላል፡፡ በሕያውነቷ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ይመሰላል፡፡ ይህች ነፍስ በሦስቱ ግብራት አንዲት ነፍስ ብትባል እንጂ ሦስት ነፍሳት እንደማትባል እግዚአብሔርንም አንድ አምላክ ነው ብለን እናምናለን እንጂ ሦስት አማልክት ነው ብለን አናምንም፡፡

2. ሁለተኛ የምጠቅሰው እያንዳንዳችን በነፍሳዊ ተፈጥሮአችንና ሥጋዊ በሆነው ደመ ነፍሳችን የተቀዳጀናቸውን ልብ፣ ቃልና እስትንፋስ የተባሉትን ረቂቃን መሣሪያዎች ነው፡፡ በልቡናችን እግዚአብሔር አብ በቃላችን እግዚአብሔር ወልድ በእስትንፋሳችን እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ይመሰላሉ ብለናል፡፡ ስለዚህ እኛ በአንድ ልቡናችን እንደምናስብ እነርሱም በእግዚአብሔር አብ ልቡናነት በአንድ ያስባሉ፡፡ እኛ በአንድ ቃላችን እንደምንነጋገር እነርሱም በእግዚአብሔር ወልድ ቃልነት በአንድነት ይናገራሉ፡፡ እኛ በአንድ እስትንፋስነት እንደምንተነፍስ እነርሱም በእግዝአብሔር መንፈስ ቅዱስ እስትንፋስነት ይተነፍሳሉ፡፡ በእነዚህ የህልውናችን መገለጫዎች በሆኑት በሦስቱ የሕይወት መሣሪያዎች ምክንያት እነዚሁኑ የያዘው ሰውነታችን ማለትም የእያንዳንዳችን እኔነት አንድ ቢባል እንጂ ሦስት እንደማይባል እንደዚሁ ሁሉ እግዚአብሔርም ምንም ለፍጥረቱ መልካም ሕይወትና የዘለዓለም ድኅነት ሲል የቸርነቱን ሥራ ሊሠራ በሦስት ስም ቢጠራ በሦስት አካል ቢገለጥና የግብር ሦስትነት ቢኖረውም አንድ አምላክ እንጂ ሦስት አማልእክት ስላልሆነ እርሱን አንድ አምላክ ነው ብለን እናምናለን እንጂ ሦስት አማልክት ያሉበት አምላክ ነው ብለን አናምንም፡፡

3. ለቅጽበት የማይለየንንና ሕይወታችን የሆነውን አየር እስኪ ለአንድት አፍታ እናስተውለው ! ለአየር ሦስት ነገሮች አሉት ፤ እነርሱም አካሉ፣ ርቀቱና ኀይሉ ናቸው፡፡ በአካሉ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ይመሰላል፡፡ ይህም አንድ አየር ቢባል እንጂ ሦስት አየሮች እንደማይባል እግዚአብሔርንም አንድ አምላክ ነው ብለን እናምናለን እንጂ ሦስት አማልእክት ነው ብለን አናምንም፡፡

4. ስለምንጭ ውኃ ደግም እናስብ ምንጭ ሦስት ነገሮች አሉት እነርሱም ነቅዑ /መፍለቂያው/ ዥረቱና ማርካቱ ናቸው፡፡ በነቅዑ እግዚአብሔር አብ ፣ በዥረቱ እግዚአብሔር ወልድ፣ በማርካቱ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ይመሰላል፡፡ የምንጭ ውኃ እንዲህ በመሆኑ አንድ ውኃ ቢባል እንጂ ሦስት ውኃዎች እንደ ማይባል እግዚአብሔርንም አንድ አምላክ ነው ብለን እናምናለን እንጂ ሦስት አማልክት ነው ብለን አናምንም፡፡

5. ፀሐይን በምሳሌነት ተመልከቷት ለፀሐይ ሦስት ነገሮች አሏት እነርሱም ክበቧ፣ ብርሃኗና ሙቀቷ ናቸው፡፡ በክበቧ እግዚአብሔር አብ፣ በብርሃኗ እግዚአብሔር ወልድ፣ በሙቀቷ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ይመሰላል፡፡ ፀሐይ እንዲህ በመሆኗ አንዲት ፀሐይ ብትባል እንጂ ሦስት ፀሐዮች እንዳማትባል እግዚአብሔርንም አንድ አምላክ ነው ብለን እናምናለን እንጂ ሦስት አማልክት ነው ብለን አናምንም፡፡

--------- ------------ ------------ ------------ ------------------------------------------------------------ ------------ ------------ 13 ኛ ገጽ ከ 33 ገጾች

ትምህርተ ሃይማኖት ርትዕት ፳፻
ዓ/ም

6. ከፍሬ ዛፎች መካከል ደግሞ የወይን ተክልን ምሳሌ እናድርግ ለወይን ሦስት ነገሮች አሉት እነርሱም ግንዱ፣ ፍሬውና ልምላሜው ናቸው፡፡
በግንዱ እግዚአብሔር አብ፣ በፍሬው እግዚአብሔር ወልድ በልምላሜው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ይመሰላል፡፡ ይህም አንድ ወይን ቢባል እንጂ ሦስት ወይኖች እንደማይባል እግዚብሔርንም አንድ አምላክ ነው ብለን እናምናለን እንጂ ሦስት አማልእክት ነው ብለን አናምንም፡፡
7. የምንኖርበትን ቤት በምሳሌነቱ እስኪ እንጠቀምበት ! ቤትን ቤት የሚያሰኙት ሦስት ነገሮች አሉ እነርሱም በግድ አንድ ሆነው መገኘት
የሚኖርባቸው መሠረቱ ፣ ግድግዳውና ጣሪያው ናቸው፡፡ በመሠረቱ እግዚአብሔር አብ፣በግድግዳው እግዚአብሔር ወልድ፣ በጣሪያው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ይመሰላል ይህም አንድ ቤት ቢባል እንጂ ሦስት ቤቶች እንደማይባል እግዚአብሔርንም አንድ አምላክ ነው ብለን እናምናለን እንጂ ሦስት አማልክት ነው ብለን አናምንም፡፡

8. እ dƒ ን እ”SMŸƒ u›"K< ›”É c=J” uvQ`¿ Zeƒ Ÿ©” ›K¨<። Ã¤¨<U ’uMvM' w`H”ና ª°Ã “†¨<::

• በፍሕሙ - ›w
• በነበልባሉ - ¨MÉ
• uª°¿ - S”ðe pÆe ÃScLK<::

2. ምስጢረ ሥጋዌ

¾ ምስጢረ YÒ« ƒUI`ƒ eK U” Áe[ÇM; u=K< ŸZe~ ›"Lƒ ›”Æ ›"M ¨MÉ u}K¾ ስሙ፣ በተለየ ›"K<፣ c¨< SJ”” Áe[ÇM::

2.1 ሥጋዌ ማለት ምን ማለት ነው

#}WÑ¨$ YÒ J’ /c¨< J’/ ŸT>K¨< ¾Ó እ´ Óe ¾¨× c=J” ƒ`Ñ<S<U YÒ SJ”' c¨< SJ” TKƒ ’¨<::

2.2 ሰው የሆነው ማን ነው;

ከሦስቱ አካላት በተለየ አካሉ ሰው የሆነው አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ ነው፡፡ ›w“ S”ðe pÆe c¨< ›MJ’<U; KU” ¨MÉ c¨< J’; ŸZe~ ›"ላት eKU” ¨MÉ w‰ }¨KÅ/c¨< J’/; u=K< ›w S”ðe pÆe u=J’< •a ¾vQ`Ã eU ¾vQ`Ã Ów` ÃóKe ’u`“ ’¨<:: U¡”Á~U ¨LÇ= ›w ን }¨LÇ=፤ ተወላዲ ወልድን ወላዲ፤ ሰራጺ S”ðe pÆe ን ›e^ç= ብንል ¾vQ`Ã eU ¾vQ`Ã Ów` ÃóKe ’u`“ ’¨<። እ”Ç=I እ”ÇÃJ” Ó” እ Ó²=›wN?` ¨MÉ uvQ`Ã eS< uvQ`Ã Ów\ KSÖ^ƒ uZe~U ðnÉ“ ሥ U[ƒ õèU c¨< J• }¨KÅ:: °w.፬፥፲፭

--------- ------------ ------------ ------------ ------------------------------------------------------------ ------------ ------------ 14 ኛ ገጽ ከ 33 ገጾች

ÉÕ “K=k "I“ƒ ¡`e„e }·ኖ Kቈ UeK Ñ>Ñ<Á” ŸS ÃÅU[’ UeK ’õc éÉn”፤ NS uðnÆ፣ ¨}kw[ uYU[~ ŸS Ÿ=Á’ Ã`Ç° ¨Ãu?´¨’ ¨MÉ }”Y› - K=k ¡`e„e "I“ት Ÿ;Ö=›}™‹“ ŸuÅK™‹ Ò` }qÖ[፤ ¾እ—” ’õe ŸéÉn” ’õe Ò` ÃÚU` ²”É (እ—”) ŸéÉn” ’õe ÃÚU[” ²”É uðnÆ ታSS፤ እ—” Ã[Ç” ²”É uS¨<ÅÆ }ku[ ÁÉነ” ²”ÉU }’X::”

**የእግዚአብሔር ወልድ ልደታት**

1. Ÿ²S“ƒ uòƒ ¯KTƒ dÃðÖ\ Ÿ እ Ó²=›wN?` ›w ÁK እ“ƒ የተወለደው የባሕርይ ልደት ¾SËS]Á¨< MÅƒ ነው። /S´.ፀያፀ፥ፎ/ መዝ. 2፥7

ÉÕ:- UeK?Ÿ kÇT© u°K} ·ነÃM uw`H•S< KpÆd” ¨KÉŸ<Ÿ እ UŸ`Y እ UpÉS ¢Ÿu êvQ= kÇT© ወልድ ሆይ! u·ነÃM k” upÆd” w`H” Ÿ›”} Ò` ’u`Ÿ< Ÿ›Øu=Á ¢Ÿw ›ekÉV ŸJÉ ¨KÉG<I:: ይላል።
ÉÕ:- ´ ¨<እ~ kÇT© ²cT°’ ¨²`›=’ ¨²Ö¾p’ ¨ዘÑWX እ Ç©’ , kÇT©¨< ÃI ’¨< kÇT©¨< c=M pÉS ¯KU Ÿ›w ÁK እ“ƒ S¨KÆ”፤ ÃI ’¨< c=M É·ነ[ ¯KU ŸÉ”ÓM T ር ÁU ÁK ›vf S¨KÆ” ’¨<። ²cT°’ ¾cT’¨< ›G<” Á¾’¨< kÇT©¨< ÃI ’¨< ÖÃk” ¾}[Ç’¨< እ Ð‰‹” ¾Ççc<ƒ Ã ሀ kÇT© ’¨<።

2. É·ነ[ ¯KU /u%EL—¨< ²S”/ Ÿ እ Su?ታ‹” ŸpÉeƒ É”ÓM T`ÁU ²S” Ÿ}qÖ[ ¯KU Ÿ}ðÖ[ u□¨k Ñ>²?“ x□ÁK ›vƒ uÉ”ÓM“ ¾}¨KÅ¨< G<K}— MÅƒ ’¨<:: />=d.ፏ፥ፗፀ'ፀ፥ፏ፣ T,.ፏ፥ፏፀ ÑL.ፀ፥ፀ'T,.ፎ፥ፗፏ T,.ፗፏ፥ፏ-ፏ/›=d ፀ፥ፏ
ድ·ነ ²Ã’ÓY Ku?} Á°qw K¯KU ¨›Mx T·ነKpf KS”ÓY~ Ç=u S”u[ Ç©ƒ ƒጸ”° S”ÓY~ K¡`e„e , K²LKS< uÁ°qw u?ƒ Ã’ÓXM KS”Ó ሥ~U õጸT@ ¾K¨<U uÇ©ƒ ዙó” LÃ ¾¡`e„e S”ÓYƒ ƒጸ“K‹::
ÉÕ ç`N ›=dÃÁe እ”² ÃwM Qí” }¨MÅ K’ ŸS ÁQÃ¨’ Sê› %u?’ ¨¨[Å እ UL ዕK< ¨}WÑ¨ ው e} T ሕ ì’ É”ÓM ¨›”fc¨ Ç=u UÉ` ¨›e}`›¾ ›UL¡ ŸS cw እ□, አ=dÃÁe እ Ç=I እ ÁK ጮ ተናገረ Qí” }¨KÅM” ÁÉ’” ²”É ¨Å— S×፣ Ÿ²<ó’<U ¨[Å uÉ”ÓM T ሕ ì” ዐÅ[ uUÉ`U }SLKc ›UL¡U እ”Åc¨< }ÑKÖ::

**አምላክ ለምን ሰው ሆነ?**

- ✓ የሰውን ልጅ በራሱ ጥፋት ከደረሰበት ሞትና ጉስቁልና ለማዳን፣
